# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፣ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 135 ታህሳስ 7 ቀን 2003 ገጽ 1


**የወቅቱ የግንቦት 7 የትግል ጥሪ**

**“የጋራ ውርደት እንዲያከትም እብሪተኞችን በጋራ እምቢ እንበል፤ ዘረኛውና አዋራጁን የወያኔ ስርዓት ለማስወገድ በጋራ እንነሳ!!!።”**

**ጥርሱን አግጦ ለወጣ የአምባገነኖች የምርጫ ለበጣ ምላሹ “እምቢ ለመብቴ!!!” ብቻ ነው**

## በዘረኛው ወያኔ እስር ቤት የሚፈጽመው አስከፊ ሰቆቃ በደህንነት እና በፖሊስ አባላት ተጋለጠ

ዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ዜጎች ላይ የሚፈጽመውን አስከፊ ሰቆቃ የሚያጋልጥ ፊር ቀዳጅ ሪፖርት በፖሊስ፣ በፌዴራል ፖሊስ እና በደህንነት አባላት ተጽፎ ይፋ መውጣቱን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት - ኢሳት - ዘግቧል።

"ከውርደት ህይወት ሞት ይሻለናል" በሚል ድፍረት በመገፋፋት ሪፖርቱን ማውጣቱን የገለጸው ቡድን፤ ሃያ አንድ ገጾች የወሰደ ሰፊ የሰቆቃ መዝገብ ማውጣቱን የኢሳት ምንጮች ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል። ሪፖርቱ፥ በተለይ በማእከላዊ እስር ቤት የኦብነግ ደጋፊዎች ናችሁ በሚል ከኦጋዴን፤ የኦነግ ደጋፊዎች በሚል ከኦሮምያ፤ እንዲሁም በ2001 አመተ ምህረት ከግንቦት 7 ጋር በመመሳጠር የመፈንቅለ መንግስት ሙከራ አድርጋችኋል ተብለው በታሰሩት ዜጎች ላይ የሚደርሱትን በብዛት ከዚህ ቀደም ተሰምተው የማያውቁ የሰቆቃ አይነቶች ዘርዝሯል።

በመፈንቅለ መንግስት ሙከራ ክስ ከታሰሩት ውስጥ አንዷ የሆኑት እና የሶስት ልጆች እናት እና የአንድ ልጅ አያት ወ/ሮ እማዋይሽ አለሙ ላይ የደረሰው ለመስማት የሚሰቀጥጥ ግፍ የማእከላዊ መርማሪዎች "እናትና እህት" የላቸውም ወይ የሚል ጥያቄ ማስነሳቱን የሪፖርቱ ጸሃፊዎች አትተዋል። መርማሪዎቹ፥ የወ/ሮ እማዋይሽን አይኖች በጨርቅ ሸፍነው እና እጆቻቸውን በካቴና አስረው ለምርመራ እንደሚወስዷቸው፤ እየሰቀሉ የውስጥ እግራቸውን፣ እጆቻቸውን፣ ታፋቸውን፣ መቀመጫቸውን እና ጀርባቸውን በቃላት ለመግለጽ በሚቸግር ጭካኔ እንደገረፏቸው፤ ልብሳቸውን አስወልቀው ጡቶቻቸው እስኪደሙ ድረስ በኤሌክትሪክ ገመድ እንደገረፏቸው የአሰቃዮቹ ባልደረቦች በጽሁፉ መስክረዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የመለስ ዜናዊ የሃብት ምዝገባ ህዝብ ማታለያ ብቻ ነው ተባለ

መለስ ዜናዊ በቅርቡ በጻደቀው የሃብት ምዝገባ አዋጅ መሰረት ንብረቱን ማስመዝገቡ ህዝብ ለማታለል የተሸረበ ሴራ ብቻ ነው ሲሉ አንድ የጸረ ሙስና ኮሚሽን ሰራተኛ ለግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ተናግረዋል።

ግለሰቡ እንደሚሉት ከሆነ፥ በኮሚሽኑ ውስጥ የአገዛዙ ሹመኞች የሆኑትን ሰዎች ጨምሮ፥ መለስ ዜናዊ እውነተኛ ሃብቱን እያስመዘገበ ነው ብሎ ያመነ የለም። "ሽር ጉዱ ሁሉ ባዱ የፕሮፓጋንዳ ስራ እንደሆነ ሁሉም ያውቀዋል፤ አብዛኛው የመለስ ዜናዊ ሃብት ያለው ከአገር ውጪ ነው። ይሁን እንጂ እንኳን ውጭ ያኖረውን አገር ውስጥ ያለውንም ሁሉን እንዲናገር የሚጠብቀውም፤ የሚጠይቀውም የለም" ብለዋል።

ግለሰቡ ጨምረውም፥ ጸረ-ሙስና ኮሚሽን ተብዬው እራሱ ሲጀመር ዘረኛው አምባገነን የፖለቲካ ተቀናቃኞቹን እና የማይደግፉትን ዘብጥያ ለመወርወር የሚጠቀምበት ተቋም እንጂ ገለልተኛ የሆነ ባለመሆኑ፣ መለስ ዜናዊን ተከታትሎ እውነት መናገሩን ያረጋግጣል የሚለው ሃሳብ ቧልት ነው ብለዋል። ኮሚሽኑ በርካታ የሙስና ጥቆማዎች እንደሚደርሱት እና የፖለቲካ መሳሪያ በመሆኑ ከመለስ ዜናዊ ትእዛዝ እስኪመጣለት ድረስ ምርመራ ለማድረግ ምንም እይነት ተነሳሽነት እንደማያደርገም ገልጸዋል። (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኦሮሚያ መንግስት ሰራተኞች በክልሉ የወያኔ ሎሌዎች ላይ ግልጽ ተቃውሞ እያሳዩ መሆኑ ታወቀ

የኦሮሚያ ክልል መንግስት ሰራተኞች በወያኔ አገዛዝ ላይ ያላቸውን ቅሬታ እና ተቃውሞ መደበቅ ከሚችሉት በላይ እየሆነባቸው እንደመጣ ሰሞኑን የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ከአዲስ አበባ አጠናቅሮ በላከው ዘገባ የኦሮሚያ ባለሥልጣኖች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በሚጠሩት የውስጥ ስብሰባ ለአመታት ታምቆ የቆየው የሰራተኞች ብሶትና እሮሮ እየገነፈለ መውጣት መጀመሩን ለማወቅ ከመቻሉም በላይ አዲሱ የክልሉ ፕሬዚደንት አለማየሁ አቶምሳ ጥቅምት 29 ቀን 2003 የጠራው ስብሰባ ባልተጠበቀ ሁኔታ ተስተጓጉሏል። ፕሬዚደንቱ የክልሉን የቢሮ ሃላፊዎች በስድስት ኪሎ በመሰብሰብ ስለ እድገት እና ትራንስፎርሜሽን፤ እንዲሁም ስለ መልካም አስተዳደር ውይይት ለማድረግ እንደሚፈልግ በመግለጽ ስብሰባውን እንደጀመረ ታውቋል። የመግቢያ ንግግሩን ካደረገ በኋላም ሰራተኞቹ በተጠቀሱት አርእስቶች ላይ አስተያየቶቻቸውን እንዲሰጡ ጥሪ አቅርቧል። ይሁን እንጂ፥ ያገኘው ምላሽ ጸጥታን ብቻ ነበር ይላል የደረሰን ዘገባ። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

**ግዜ** ግንቦት 7 ዜና

## ዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ በቴሌ ሰራተኞች ክፉኛ ተወገዘ

በኢትዮጵያ ቴሌኮሚውኒኬሽን ኮርፖሬሽን ሰራተኞች እንደተጻፈ የሚነገርለት እና ባለፈው ሳምንት 'ፍትህ' ለተባለው ጋዜጣ የተላከ ደብዳቤ ዘረኛውን አምባገነን መለስ ዜናዊን ክፉኛ አውግዟል።

ደብዳቤው መለስን "አንድ ጠብታ ፍሬ የማይወጣው ስብሰባ የሚሰበስብና የሚበትን"፣ "የህዝቦችን ጩኸት የሚያይበትና የሚያደምጥበት ግዜና ሞራላዊ ጥንካሬ የሌለው" ነው ይለዋል። በሺዎች የሚቆጠሩ የኮርፖሬሽኑ ሰራተኞች ስራቸው አደጋ ላይ እንደሚገኝ እና ከነቤተሰቦቻቸው ለረሃብ መጋለጣቸውን የሚገልጸው ደብዳቤ፤ ኩባንያው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ ስልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ የባሰውኑ ኋላ ቀር እንደሆነና ብቃት በሌላቸው ካድሬዎች እንደተሞላ ይናገራል። የደብዳቤው ጸሃፊዎች፥ በመለስ አገዛዝ ስር ድርጅቱን የማሳደጉ ስራ በዘረፋ እንደተተካ ተችተው፤ አዳዲስ የተሾሙትን ካድሬዎች "እጃቸው ለስርቆት እና ምላሳቸው ለወሬ የረዘመ" ብሎአቸዋል።

ቀድሞ የኮርፖሬሽኑ ቦርድ ሰብሳቢ የነበረውና አሁን በመለስ ዜናዊ የትራንስፖርት እና ኮሚኒኬሽን ሚኒስቴር ተደርጎ የተሾመው ደብረጽዮንም ክፉኛ ተተችቷል። ጸሃፊዎቹ በኮርፖሬሽኑ ውስጥ ለተሰንራፋው ሙስና እና ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ለሚፈናቀሉት ሰራተኞች ሁሉ ሃላፊነቱን በሱ ትከሻ ላይ አኑረዋል። ጨምረውም፥ አገዛዙ ኮርፖሬሽኑ በውጭ ኩባንያ እንዲተዳደር አሳልፎ መስጠቱን አውግዘዋል። እንደ ሰራተኞቹ ገለጻ፥ ድርጅቱ ወዳለበት ዝቅተኛ ደረጃ የደረሰው ብቁ ኢትዮጵያውያን ባለሙያዎች ጠፍተው ሳይሆን፤ እነዛ ባለሙያዎች እየተገፉ ብቃት በሌላቸው ካድሬዎች በመተካታቸው ነው።

የደብዳቤው ጸሃፊዎች፥ ይህንን ሁሉ ትችት በመለስ ዜናዊ እና በአገዛዙ ላይ ካደረጉ በኋላ ግን እሱኑ መልሶ ጣልቃ በመግባት ስራቸውን እንዲያድንላቸው ተማጽነዋል።

## እየተባባሰ የመጣው ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች በአድስ አበባ ከተማ ውስጥ ውጥረትን ፈጥሯል

የሃይል እጥረት፣ የኑሮ ውድነት፣ የአንዳንድ ምርቶች ከገበያ ላይ መጥፋት፣ የትራንስፖርት ችግር እና የደህንነት ጉዳዮች አዲስ አበባን ከጊዜ ወደጊዜ እየተባባሰ በሄደ ውጥረት ውስጥ ከተዋታል ስትል የግንቦት 7 ድምጽ ሪፖርተር ለዝግጅት ክፍላችን ባስተላለፈችው ዘገባ ገልጻለች።

በከተማይቱ ያለው የኤሌክትሪክ ሃይል እጥረት የከፋ ደረጃ ላይ ከመድረሱ የተነሳ ወፍጮ ቤቶች ሳይቀሩ ከተወሰኑ ሰአታት በኋላ እንዳይሰሩ እየተከለከሉ እንደሆነ ዘገባው አመልክቷል። የኑሮ ውድነት ህዝቡን ለከፍተኛ ጭንቀት እና በርካቶችን ለረሃብ ከማጋለጡ በተጨማሪ አገዛዙን እርቃን እንዳወጣውም ዘጋቢያችን ከላከቺው ሪፖርት ለመረዳት ተችሎአል ። በየቀኑ ገበያ በመውጣት እህል ምን ያህል መወደዱን የሚያውቀው ህዝቡ ሆኖ ሳለ በወያኔ ቁጥጥር ስር የሚገኙ መገናኛ ብዙሃን ዋጋ አሳንሰው እና ንረቱ እንደቀነሰ አድርገው መናገራቸው አገዛዙ በህብረተሰቡ ውስጥ የባሰ እንዲዋረድ እያደረገው መሆኑን በርካቶች ይስማማሉ።

በተለያዩ ምክንያቶች ምርቶች ከገበያ ላይ እየጠፉ እንደሆነም የታወቀ ሲሆን፤ ከሰሞኑ ሙዝ እና ቲማቲም ማግኘት ጭራሹን እንዳልተቻለ፤ ይሁን እንጂ ህዝቡን ከገጠሙት ችግሮች ይኸኛው ትንሹ መሆኑን ዘገባው አመልክቷል። ለረዥም ጊዜ መፍትሄ አጥቶ የቆየው የከተማይቱ የትራንስፖርት ችግር በተለይ የመንግስት ሰራተኞችን ለእንግልት እና ለጭንቀት እየዳረገ ነውም ተብሎአል። (ወደ ገጽ 3 ዞሯል)

## በደቡብ አውስትራሊያ በምትገኘው አደላይድ ከተማ የድህረ ምርጫ 97 ሰማእታት ታስበው ዋሉ

በደቡብ አውስትራሊያ በምትገኘው አደላይድ ከተማ የድህረ ምርጫ 97 ሰማእታት መታሰቢያ በአል መከበሩን ከስፍራው የደረሰን ዘገባ አመልክቷል።

የዝግጅቱ አስተባባሪዎች የግንቦት 7 ድምጽን የዝግጅት ክፍል ጨምሮ ለበርካታ መገናኛ ብዙሃን የላኩት ሪፖርት፤ ቅዳሜ ታህሳስ 3 ቀን በተካሄደው የመታሰቢያ በአል ላይ ምርጫውን ተከትሎ የነበረውን ሁኔታ ለማስረዳት ይሆን ዘንድ የተዘጋጀው የፊልምና የፎቶግራፍ ቅንብር ታዳሚውን እንባ አራጭቷል ይላል።

የበአሉን አስተባባሪዎች በመወከል ዝግጅቱን በንግግር የከፈቱት አቶ መኮነን ምስጋናው፡- "ባለንበት ዘመን የእውነትን ታላቅነት የሚያምኑ በርካቶች ቢኖሩም ለእውነት የሚቆሙት፤ አልፎ ተርፎም መስዋእትነት የሚከፍሉት ጥቂቶች ናቸው። እኛም ዛሬ የተሰባሰብነው ከ80 ሚሊዮን የአገራችን ህዝብ ጋር ሲነጻጸሩ ከቁጥር የማይገቡ በግፍ የተገደሉ ወገኖቻችንን ለማሰብ ነው። እነዚህ ሰዎች ትናንት አፈር ቢለብሱም፣ ስማቸው እና ታሪካቸው ግን ምንጊዜም ህያው ነው" ብለዋል።

በዝግጅቱ ላይ በስልክ ንግግር ያደረጉት የቀድሞው የህወሃት (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የትግራይ ገዢ ጉጅሌ የበላይነትን ማንገስ ከፌደራሊዝም ጋር የሚያገናኘው ነገር የለም

ሰሞኑን በአንድ በኩል ረሃብና ችጋር፤ በሌላ በኩል ደግሞ ጥጋብና ድግስ አዲስ አበባን እያናወጧት ነው። የትግራይ ገዥ ጉጅሌ በወረራ በያዛቸው ቦታዎች ሁሉ ድግስ እያዘጋጀ ቢሆንም የአዲስ አበባው ግን ልዩ ነው። የየክልሉ ምስለኔዎችና ከአምስት መቶ በላይ የውጭ አገር እንግዶች ለዚህ ድግስ ተጋብዘዋል። የድግሱ መጠሪያ "የፌደራሊዝም ኮንፍረስ" ተብሏል።

የድግሱ መርሃ ግብር የሚከተለውን ይመስላል -

- በቅድሚያ ነፃነታቸውን የተገፈፉ፤ በገዛ አገራቸው ሁለተኛና ሶስተኛ ዜጋ የሆኑ የኅበረተሰብ ክፍሎች በትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ምስለኔዎች መረገጣቸው የፈጠረላቸውን ደስታ ይገልፃሉ፤
- ቀጥሎ መሬታቸው ተነጥቆ ለቱጃሮች የታደሉባቸው ገበሬዎችም ኑሯቸው ምን ያህል እንደተሻሻለ በዚሁ መድረክ ምስክርነት ይሰጣሉ፤
- ቀጥሎ ደግሞ የአካዳሚ ነፃነት የተነፈጉ ምሁራን የአንድን ዘር የበላይነት ማስፈን እንዴት የህዝቦችን እኩልነት እንዳመጣ ይተነትናሉ፤
- ከየክልሉ የመጡ ምስለኔዎች ደግሞ ወያኔ የፈለሰፈው ፌደራሊዝም ታይቶ ተሰምቶ የማይታወቅ ምትሃት የተላበሰ ስለመሆኑ ማስረጃዎችን ከየክልላቸው ነባራዊ ሁኔታዎች ጋር እያጣቀሱ ያብራራሉ፤
- ከእውነት እጅግ የራቁና የተጋነኑ የደስታ መግለጫዎች፣ የውሸት መረጃዎች እና የውሸት ዲስኩሮች ይደመጣሉ፤

በመጨረሻ በዘር ማጥፋት ወንጀል ተከሰው እየተፈለጉ ያሉት የሱዳኑ አልበሽር ፣ መለስ ከእሳቸው እሳቸው ደግሞ ከመለስ ስለተማሯቸው ጥበቦች በመናገር ድግሱን ይባርካሉ።

በዚህ ድግስ ብዙ ይበላል፤ ብዙ ይጠጣል። የብሄር ብሄረሰቦች የባህል ዘፈኖች በብዛት ይቀርባሉ። የእነዚህ ዘፈኖች መዘፈን የፊደራሊዝም ሥር መስደድ አመላካቾች ናቸው።

በልመና የሚተዳደሩ ድሆች ግን የድግሱ ተካፋዮች አይሆኑም። "ፊዴራሊዝም" በኢትዮጵያ ያመጣው እውነተኛ ውጤት ህያው ማስረጃዎች ናቸውና እንኳንስ እድግሱ ውስጥ በድግሱ ወቅት በከተማው ውስጥ እንዲገኙ አይፈቀድም። በዚህም ምክንያት ከሳምንት በፊት ተለቃቅመው ከከተማ ውጭ ተጥለዋል።

ኢትዮጵያዊያን እንዲህ ዓይነቱን ውሸት ለሃያ ዓመታት ስንሰማ በመክረማችን ሰልችቶናል። ሃቁ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ወርሮ የያዘውን አገር ከራሱ ብቻ በወጡ ሰዎች በሚመራ ሠራዊትና የስለላ ተቋም አማካይነት እየገዛ፤ ሃብቱን እየመዘበረ መሆኑ ነው። ይህንን የብዝበዛ ሥርዓትን ነው በየአካባቢው ለመለመላቸው ተላላኪዎቹ የይስሙላ ሹመት እየሰጠና የተጋጠ አጥንት እየጣለ "ፊደራሊዝም" እያለ የሚጠራው። ይባስ ብሎ በህዝብ ብዛትም ሆነ በመሬት ስፋት ከፍተኛው ድርሻ የያዙት የኅብረተሰብ ክፍሎች በይስሙላ ስልጣን ሳይቀር እየተገፉ አነስተኞቹ በብዙሃኑ ላይ የተሾሙበት ሥርዓትን ነው "ፌደራሊዝም" ብሎ የሚጠራው።

በተለያዩ የኅብረተሰባችን ክፍሎች መካከል ያለው ቅራኔ እጅግ አስጊ የሆነ ደረጃ ላይ ደርሶ እየታየና ዘር ለይቶ መቧደን እና መቧቀስ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ባህል እየሆነ መምጣቱ በግልጽ እየተስተዋለ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ ግን ስለብሄር ብሄረሰቦች መፋቀር መደስኮሩን ሥራዬ ብሎ ተያይዞታል። ወያኔ በስሙ በሚነግድበት ሰፊው የትግራይ እና በተቀረው የኢትዮጵያ ህዝብ መካከል ስር እየሰደደ የመጣው ቅራኔ አገራችን የት ያደርሳት ይሆን የሚለው ስጋት ከኢትዮጵያዊያን አልፎ የውጭ አገር ሰዎችን እያሳሰበ ባለበት ባሁኑ ወቅት ነው ወያኔ ስላስተሳሰራት ኢትዮጵያ መራቀቅ እነ መለስ ተከነውበታል። የትግራይ ገዥ ጉጅሌ የጠፈጠፈው "ፌደራሊዝም" በማር የተለወሰ መርዝ መሆኑ ባለፉት ሃያ አመታት በተግባር ያየነው ጉዳይ ነው። የሆድ ጉዳይ ሆኖባቸው ነው እንጂ የገዥው ጉጅሌ ምስለኔዎችና ተላላኪዎችም ይህንን ያውቃሉ ብለን እናምናለን።

ወያኔና ፌደራሊዝም እሳትና ጭድ ናቸው። በዚህም ምክንያት ነው እውነተኛውን ፊደራሊዝም ለመከላከል የውሸት ፊደራሊዝም ገንብቶ፤ እኩልነትን አረግጦ፣ ነፃነታችን ገፍፎ፤ ሃብታችንን እየመዘበረ የሚሳለቅብን። በአጭር ጊዜ ውስጥ የትግራዩን ገዢ ጉጅሌ ከሥልጣን ካላባረርን የደቡብ አፍሪካ ዜጎች ከ15 ዓመታት በፊት የተገላገሉት የአፓርታይድ ፌደራሊዝም ለልጆቻችንና ለመጪው ትውልድ ማውረሳችን የማይቀር ነው።

ግንቦት 7: የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ ለነፃነትና ለፍትህ የምናደረገው ትግል አንዱ ግብ የትግራይ ገዢ ጉጅሌ የቀመመልንን መርዘኛና ዘረኛ ፌደራሊዝምን ማስወገድ እና በምትኩም በእኩልነት ላይ የተገነባ ዲሞክራሲያዊ ፌደራሊዝም ሥራ ላይ ማዋል መሆኑን ተገንዝበን ትግላችን እናፋፍም ይላል። በፌደራሊዝም ስም ዘረኝነትን ማስፋፋትና አንድ ዘር የሌሎች የበላይነት ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት የመግታት ኃላፊነት የኛ ነው።

**ድል ለኢትዮጵያ ሕዝብ!!!**

●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●●

### በዘረኛው ወያኔ እስር ቤት የሚፈጽመው አስከፊ ሰቆቃ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በወ/ሮ እማዋይሽ ላይ የደረሰው ግርፋት የቀሰቀሰው ስቃይ እና ህመም ወደ ቃሊቲ ከወረዱ በኋላም እንዳላቆመ እና አሁንም የሚኖሩት የስቃይ ማስታገሻ ክኒን እየዋጡ እንደሆነ ታውቋል። እናቲቱ ስቃያቸውን ለማስቆም ሲሉ ገራፊዎቻቸው በፈለጉት ኑዛዜ ላይ መፈረማቸውም በዘገባው ተገልጿል።

እንደ ምሳሌ ከተጠቀሱት ውስጥ፥ አቶ ሃሰን የሚባል እና ከደጋሃቡር ታፍኖ የመጣ ኦጋዴኒ ፍርድ ቤት ሳይቀርብ በእስር በቆየባቸው ሁለት አመታት፤ ለስድስት ወራት ሙሉ እጁ በካቴና፣ እግሩ በብረት ታስሮ እንደቆየ፤ በድብደባ ብዛት የግራ ዘር ፍሬው ማሙቶ እንደጠፋ ለማወቅ ተችሏል። ሪፖርቱ፥ "እንደ ከብት የወንድን ልጅ ብልት በመቀጥቀጥ ዘር አልባ ማድረግ በዛ ክፉ በሚባለው የደርግ ግዜ እንኳን ያልነበረ ነበር።" እንደሚል ኢሳት ገልጿል።

ከነቀምት፣ ከአምቦ፣ ከምስራቅ ሀረርጌ እና ከከሚሴ ታፍነው መጥተው ማእከላዊ ምርመራ ጣቢያ ከ6 ወራት በላይ ከፍተኛ ስቃይ 13 አሮሞ ወጣቶችም ሪፖርቱ ይናገራል። "እጃቸው በካቴና ታስሮ በግድግዳ ላይ ይሰቀላሉ፣ ይዘቀዘቃሉ፣ በኤሌክትሪክ ይገረፋሉ። ከነዚህ መሃል ሶስቱ ብልታቸው ላይ በደረሰባቸው ግርፋት ምክንያት ሽንታቸውን መቆጣጠር አይችሉም። አንዳንዶቹ ብልታቸው ላይ በደረሰባቸው ግርፋት የተነሳ ተኮላሽተዋል። አንዳንዶቹ አካላቸው ጎድሏል፤ አይናቸው ጠፍቷል፤ እጃቸው ተሰብሯል፤ ጥፍራቸው ተነቅሏል። ከአስራ ሶስቱ መሃል ሁለቱ በሰርጋቸው እለት ነው የታፈኑት። ከእነዚህም ሌላ እጃቸውንና እግራቸውን በካቴና ታስረው ቀንም ለሊትም በጨለማ ቤት ውስጥ ተዘግቶባቸው እዛው እስር ቤት ውስጥ የሚኖሩት ሁለት እድሜያቸው ከ15 አመት በታች የሆኑ ወጣት ልጆች አሉ።" ይላል።

በዚህ የሰቆቃ መዝገብ ውስጥ የበርካታ እስረኞች ስም እና የደረሰባቸው ግፍ ዝርዝር መገለጹን የኢሳት ምንጮቻችን ገልጸዋል።

የግንቦት 7 ድምጽ የመረጃውን ሙሉ መልዕክት ከሚቀጥለው እትም ጀምሮ ለህዝብ ያቀርባል

### በደቡብ አውስትራሊያ በምትገኘው አደላይድ ከተማ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የፋይናንስ ክፍል ሃላፊ አቶ ገብረመድህን አራያ፥ ባደረጉት ንግግር ወያኔ የህዝብ ውክልና የሌለው ዘረኛና አገር የማፍረስ አጀንዳውን እየተገበረ ያለ ጸረ አገር ቡድን ነው ካሉ ቦኋላ "ሁሉም ኢትዮጵያዊ በአንድ ግንባር ስር ተሰባስቦ ወያኔን መዋጋት አለበት" ብለዋል።

### የመለስ ዜናዊ የሃብት ምዝገባ ህዝብ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

የአገዛዙ መገናኛ ብዙሃን የሆነው ዋልታ ኢንፎርሜሽን ማእከል ባለፈው ሳምንት ባስተላለፈው ዘገባ፥ የጸረ-ሙስና ኮሚሽነር የመለስን ሃብት ማስመዝገብ አስመልክቶ አዲስ ስለወጣው አዋጅ ሲናገር፥ አዋጁ የሃገር ንብረት በባበልስጣናት እጅ ነው ያለው የሚለውን አስተሳሰብ እንደሚያስወግድ እና በህዝብ ዘንድ አመኔታን ለመፍጠር እንደሚረዳ ተናግሯል።

ዘጋቢያችንን ያናገሩት ምንጭ እንደሚሉትም፥ በሳቸው ቋንቋ "ይህ ሁሉ ድራማና ሸር ጉድ" የሚካሄደው ህዝብን አታሎ አመኔታ ለማግኘት ነው። ይሁን እንጂ የባለስልጣናቱ ሙስና ወሬ ብቻ ሳይሆን ህዝቡ በአይኑ የሚያየው ጉዳይ ስለሆነ፤ ሙከራቸው ከንቱ ነው ብለዋል።

በአዲሱ የወያኔ ካቢኔ ውስጥ የውጭ ጉዳይ ምንስቴር ዴታ ሆኖ የተሾመው ብርሃኔ ገብረክርስቶስ በአሜሪካ የወያኔ አምባሳደር ሆኖ ይሰራ በነበረበት ወቅት ከባለቤቱ ጋር በነበረበት የ40 ሚሊዮን ዶላር ንብረት ክፍፍል ክርክር ገንዘቡ የራሱ ሳይሆን የመለስ ዜናዊ እንደሆነ ፍርድ ቤት ቀርቦ ማስረዳቱ ሲታወቅ ፊይናንሻል ታየምስ የተባለው አንድ የ እንግሊዝ ጋዜጣ በ1998 አም ውስጥ መለስ በዩናይትድ ክንግደም ባንክ ውስጥ ከ80 ሚሊዮን ፓውንድ በላይ ገንዘብ አንዳለው ዘግቦ እንደነበር ይታወሳል። መለስ ዜናዊ አሁን አስመዘገበ በተባለው ንብረት ውስጥ ይህ ገንዘብ አንዳልሰፈረ ውስጥ አዋቂ ምንጮች ይናገራሉ።

ለአገዛዙ ቅርብ የሆነው ሪፖርተር ግዜጣ ባለፈው ሳምንት ለንባብ ባበቃው ህትመት ፣ በዚሁ ሸር ጉድ እንኳ እስካሁን የተሳተፉት አራት ባለስልጣናት ብቻ መሆናቸውን ገልጿል።

## መለስን መፋረድ እንጂ መለማመጥ ቱርፋት የለውም

የኢትዮጵያ ቴሌኮሚውኒኬሽን ኮርፖሬሽን ሰራተኞች ነን የሚሉ ሰዎች ባለፈው ሳምንት ጽፈው ለፍትህ ጋዜጣ ልከውታል በተባለ ደብዳቤ፣ ለዘረኛው አምባገነን መለስ ዜናዊ የሚገባውን ትችት ሰጥተውታል። "አንድ ጠብታ ፍሬ የማይወጣው ስብሰባ የሚሰበስብና የሚበትን"፣ "የህዝቦችን ጩኸት የሚያይበትና የሚያደምጥበት ግዜና ሞራላዊ ጥንካሬ የሌለው"፤ እና "በሚቆጣጠረው ጦር ህዝቡን አፍኖ የሚገዛ አምባገነን" ብለውታል። በአገሪቱ ከተነሱት አምባገነኖች ውስጥ አንዱ እንደሆነም ነግረውታል።

ብቁ ባለሙያዎችን ከመንግስት ድርጅቶች እየገፉ አስወጥቶ በነሱ አባባል "እንኳን ስራቸውን እራሳቸውንም በማያውቁ" ካድሬዎች መሙላቱን፤ በዚህም ምክንያት በብዙ ቢሊዮን ብር የሚቆጠር ትርፍ የሚያስገኘው የህዝብ ኩባንያ መንኮታኮቱን ደብዳቤው አትቷል። ይኸም ሆኖ ግን ድርጅቱ ትርፋማነቱን እንዳላጣ፤ ነገር ግን ለዘረፋ እና ለብኩንነት የተጋለጠ እንደሆነም መስክረዋል።

አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ ያለውን አፈና ከግምት በማስገባት፣ እንዲህ ያለ ደብዳቤ በገለልተኛ አካላት ምንም ሽረባ እና ተንኮል ከበስተጀርባው ሳይኖርበት በግልጽ መውጣቱ የሚያስገርም ነው። ይህ ጽሁፍ የድርጅቱን ሰራተኞች ለማጥመድ ያልተሸረበ ሴራ እና እውነተኛ ከሆነም ጸሃፊዎቹ ለድፍረታቸው ሊደነቁ ይገባቸዋል።

በርግጥ ዘረኛው አምባገነን መለስ እንዲህ አይነቱ ትችት ሲያንሰበት ነው። "ሲያንስበት" ነው ስንል ቀልድ ይመስላል። መለስ ዜናዊን አሁን የሚገባው ትችት ሳይሆን ቅጣት ነው። ሁለት እጆቹ በጀርባው በኩል በብረት ካቴና ተከርችመው ፍርድ ፊት መቆም ይገባዋል። ላስገደላቸው ህጻናት እና እናቶች በህግ ፊት ዋጋ ሊከፍል ይገባዋል። የትችት ዘመን ካለፈ ሰነባብቷል።

ይልቅስ እኛን የገረመን፣ እንኳን እንደዚህ በቁጣ የሚጽፉ ይቅሩና፣ በትህትና የመከሩ ሳይቀሩ እስር ቤት በሚወርዱባት አገር እነዚህ "ኑሯችን ለአደጋ ተጋልጧል" የሚሉ ሰራተኞች ምሬታቸውን በግልጽ መግለጻቸው ነው። በርግጥም፥ ህዝቡ እየደረሰበት ስላለው መከራ መታገሱን እንዳቆመ እያሳዩ ካሉት ምልክቶች ውስጥ አንዱ ነው። ለቴሌ ሰራተኞች፣ ይበለው እንላለን።

ይሁን እንጂ አንድ ሳንጠቅሰው የማናልፈው ነጥብም አለ። የደብዳቤው ጸሃፊዎች፥ መለስ ዜናዊን ክፉኛ አውግዘው የህዝብ ጩኸት መስማት የማይችል አምባገነን መሆኑን ከነገሩት በኋላ፤ በድርጅታቸው ውስጥ ለሚካሄደው የተበላሸ አሰራርም በዋነኛነት ተጠያቂው እሱ መሆኑን ከጠቆሙ በኋላ፤ እሱው እራሱ መልሶ ከተጋፈጡት አደጋ እንዲያድናቸው ይማጸኑታል። ከሳጥናኤል የነፍስ ምህረትን እንደመለመን ሆኖ አግኝተነዋል።

መለስ ዜናዊ፥ የህዝብን ጩኸት እንዳይሰማ እና አገሪቱን እንደ ወንበዴ እንጂ እንደ ህዝብ አገልጋይ እንዳይመራ የሚከለክለው መሰረታዊ እንቅፋት አለበት። ይኸም፥ በፋሽስት ጣሊያን ወረራ ወቅት ለባንዳ አድረው አገር ለመሸጥ ካልተሳካላቸው ቤተሰብ አብራክ የወጣ መሆኑና በትግራይ ተጋዳላይ ጉያ ውስጥ ተወሽቆ የመንግስትን በትረ ሥልጣን በጉልበት ለመቆጣጠር የበቃ ፣ ዘረኛ፣ ጸረ-አገር እና በጥላቻ የተሞላ ግለሰብ መሆኑ ነው። እንዲህ አይነት ጸረ አገር ስሜት በደም ሥሩ ውስጥ የተቀበረ ግለሰብ ደግሞ አገር ይከፋፍል፤ ይሰርቅ፣ ይዘርፍ፣ ይገድል እና ህገ-ወጥ በሆነ መንገድ ያስር ይሆን እንጂ፤ አያንጽም፣ አይገነባም፣ መልካምን አያደርግም። እንደዛ የሚያደርግ መስሎ ቢታይ የቁጥጥር ዘመኑን ለማራዘም ሲል ጭንብል ለብሶ እንጂ ከልቡ አይደለም።

መለስ ዜናዊ በህዝብ የተፈጠረ እና ለህዝብ የቆመ መንግስት ቁንጮ ሳይሆን፤ በህገ-ወጥ መንገድ የሚገዛ የወንበዴዎች ቡድን መሪ ነው። እንዲህ ካለው ሰው ዘንድ ምህረትን መማጸን፣ ሰማይ ዝቅ እንዲል ፤ በሬ እንዲወልድ፤ ነጭ ጥቁር እንዲሆን፤ መመኘት ነው።

ታዲያ ለቴሌ ሰራተኞች የምንለከው ወንድማዊ ምክር፥ ነጻነታቸውን በነፈጋቸው፤ የሚገባቸውንም ከቀማቸው የወንበዴዎች ቁንጮ ፊት ወድቆ ፍትህን መለመን ትርጉም የሌለው ጉዳይ መሆኑን ተገንዝበው፤ ይህ ወንጀለኛ የሚጠይቁትን ቢሰጣቸው እንኳ ለማታለያ እና ለጊዜ መግዣነት የሚውል ጊዜያዊ መፍትሄ መሆኑን ተረድተው፤ መሰረታዊ ለውጥ ለማምጣት የሚደረገውን ትግል እንዲቀላቀሉ ነው። ዘር እና የፖለቲካ ታማኝነት ሳይሆኑ ብቃት እና ሙያ የዜጎችን የስራ ምድብ የሚወስኑባትን ኢትዮጵያ ለመገንባት የሚደረገውን ትግል እንዲያግዙ ነው። እንደ መለስ ዜናዊ ያሉትን የመከራቸውን አስኪያጆች ፍርድ ፊት ለማስቆም በሚደረገው ትግል እንዲሳተፉ ነው።

## የኦሮሚያ መንግስት ሰራተኞች በክልሉ የወያኔ ሎሌዎች . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ከወያኔ አለቆቹ ተቀብሎ ወደታች እንዲያስተላልፍ የተሰጠውን መልዕክት እንደጨረሰ ከተሰብሳቢው ሞቅ ያለ ተሳትፎ ጠብቆ የነበረው አዲሱ የክልሉ ፕረዝዳንት በቤቱ ውስጥ በሰፈነው ዝምታ እጅግ ግራ በመጋባቱ በንዴት ገንፍሎ "እኔ ውይይት ላካሄድ እንጂ መልክት ልነግራችሁ አልመጣሁምና ተናገሩ" ሲል ተሰብሳቢዎቹን በሃይለ ቃል መናገሩን ሪፖርተራችን ጠቅሶአል። ዘጋቢያችንን ያናገሩት አንድ የስብሰባው ተካፋይ "የክልሉ የቢሮ ሃላፊዎች እንደ ቦምብ የፈነዱት በዚህ ጊዜ ነበር" ሲሉ ተከትሎ የሆነውን ነገር ገልጸውታል። በዚህ ምክንያት ስለ ቀጣዮቹ አምስት አመታት ለመነጋገር የተጠራው ስብሰባ ከዛ ነጥብ በኋላ ወደ ሰራተኞች ምሬት መግለጫ ተለውጦ መስተጓጎሉን ለማወቅ ተችሎአል። ሰራተኞቹ፥ ስለ ኑሮ ውድነት፣ ስለ ሙስና እና ስለ ክልል መንግስቱ ብቃት ማነስ በማንሳት ስሞታቸውን ገልጸዋል።

ስብሰባው ከመስተጓጎሉ በፊት በርካታ ሰራተኞች በኑሮ ውድነት ምክንያት የሚኖሩት ከእጅ ወደአፍ መሆኑን እና ይኸም በህይወት እና በስራቸው ላይ ከፍተኛ ጫና ፈጥሮ እንዳለ በመናገር አማረዋል። የኖሯቸው ሁኔታ ይሄ ሆኖ ሳለም የክልሉ መንግስት በስድስት ወራት ውስጥ ኮንዶሚኒየም ቤቶች እሰጣችኋለሁ ብሎ ያለ የሌለ ገንዘባቸውን ሰብስቦ እንደወሰደ፤ ያ ከሆነ ግን ሁለት አመታት መቆጠራቸውን በምሬት ሲናገሩ ተስተውሎአል ።

ከባለ ስልጣናት ጋር በመመሳጠር የተሻለ የስራ ምድብ ማግኘት እና ውሳኔዎችን ማስቀየር የተለመደ አሰራር ነው ያሉት ተሰብሳቢዎች፤ ይህ አይነቱ አድሏዊ አሰራር በነገሰበት ስለ መልካም አስተዳደር ማውራቱ እንዳልገባቸው ገልጸዋል። ጨምረውም፥ በርግጥም በክልሉ ፕሬዚደንት እና በመሰሎቹ ላይ ባነጣጠረ መልኩ፥ የተለያዩ ችግሮች በህዝቡ ላይ የፈጠሩትን ቁስል ማየት የሚችሉት አብረው በድህነት መቀመቅ ውስጥ የሚገኙት እንደነሱ ያሉ ሰራተኞች እንጂ፤ ሁለትና ሶስት መኖሪያ ቤቶች አስገንብተው እና የህዝብ መሬት ሸጠው ባካበቱት ሃብት ምቾታቸው ከልክ ያለፈው ባለስልጣናት አይደሉም ሲሉ ክፉኛ አውግዘዋል።

የስብሰባው ተካፋዮች በመጨረሻም፥ እነዚህ ችግሮች ባሉበት ስለ ትራንስፎርሜሽን እና መልካም አስተዳደር ማውራት እንደማይችሉ አስረግጠዋል። ክልሉን አስረግጦ እንዲያስገዛ በወያኔ የተሾመው አለማየሁም ከዋና ርእሱ ወጥቶ የሰራተኞቹን ጥያቄዎች ለመመለስ መገደዱን ዘጋቢያችን ከላከልን ዜና ለማወቅ ተችሎአል።

የኦሮሚያ ክልል ሰራተኞች በየቦታው በአገዛዙ ላይ ያላቸውን ጥላቻ እና ንቀት መግለጻቸውን እንደቀጠሉም ለግንቦት 7 ዜና ምንጭ ቅርብ የሆኑ ሰዎች ይናገራሉ። ባለፈው ሳምንት ይኸው የክልሉ ፕሬዚደንት በቢሮው አካባቢ ያሉ ሰራተኞችን ሰብስቦ፥ ትራንስፎርሜሽን ማለት የውጭ ወራሪን እንደ መዋጋት ነው፤ በዚህ ውጊያ ውስጥ ደግሞ መስዋእትነት ሊኖር ይችላል ሲል ንግግር አድርጓል። ከተሰብሳቢዎቹ አንዱ ሲመልስም፥ "እንግዲህ እንደዚህ አይነት ጦርነት ውስጥ የሚገቡት የህዝብ ስጋ በልተው አጥንቱን የቆረጠሙት መሆን አለባቸው፤ እኛ ስጋችን ተበልቶ አጥንታችን የተቆረጠመውማ በምን አቅማችን" ብሎ እንደተሳለቀበት አንድ የውስጥ አዋቂ ምንጭ ለዘጋቢያችን መናገራቸውን ተያይዞ የደረሰን ዘገባ ያረጋግጣል።

## እየተባባሰ የመጣው ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ይህ በእንዲህ እንዳለ በመዲናይቱ ከዚህ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ ሁኔታ፥ ከሰሞኑ በኦርቶዶክስ እና በፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች መካከል በተፈጠረ ችግር ምክንያት በአንዳንድ ቦታዎች የመካረር ችግር እንደተፈጠረ እና አንድ ቀን ሊፈነዳ በሚችል መንገድ ታምቆ እንዳለ ለማወቅ ተችሏል። የተቀሰቀሰው ችግር ምን እንደሆነ ሙሉ በሙሉ ባይታወቅም፤ አንዲት የፕሮቴስታንት ቤተክርስቲያን በፌዴራል ፖሊስ ተከባ መደበኛ የአምልኮ ዝግጅትቷን አካሄዳለች።

ሪፖርተራችንን ያናገሩ አንድ ግለሰብ፥ የወያኔ አገዛዝ በተለያዩ ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ግጭት የመፍጠር ታሪክ እንዳለው አስታውሰው፤ ህዝብ እየደረሰበት ባለው ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ተማሮ በአገዛዙ ላይ በህብረት እንዳይነሳ የህዝቡን ሃሳብ ለመከፋፈል ሆን ተብሎ የተወጠነ ሴራ ሊሆን ይችላል ሲሉ ግምታቸውን ገልጸዋል።

## የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ያለውን የሃይል እጥረት ቀውስ ለመፍታት ተስኖታል

ባለፈው ሐምሌ ወር የግልገል ጊቤ ሁለት ግድብን ጠግኖ ጨርሶ በመስከረም ወር ሃይል ወደ ጅቡቲ ማስተላለፍ እንደሚጀምር ቃል ገብቶ ሳይሳካለት የቀረው የወያኔ አገዛዝ፤ ባለፈው ሳምንት በሰጠው ቃል ደግሞ ጥገናውን በዚህ በታህሳስ ወር ጨርሶ የፈረንጆቹ አመት ሳያልቅ የኤሌክትሪክ ሃይል ወደ ጅቢቱ መላክ እንደሚጀምር ገልጿል።

በኢትዮጵያ ኤሌክትሪክ ሃይል ኮርፖሬሽን ሹመኛ የሆነው መኩሪያ ለማ ለብሉምበርግ ዜና እንደተናገረው፤ ሃይል ለጎረቤት አገራት የመሸጡ እቅድ ለአገዛዙ ቢሳካለት፤ የሚላከው መጠን የሚወሰነው አገሪቱ ተጠቅማበት የሚተርፋት ነው ብሎአል። የወያኔው ሹመኛ በሰጠው ሃሳብ የማይስማሙ በርካታ ዜጎች ላለፉት አመታት ከፍተኛ የሆነ የመብራት ሃይል ውስጥ እየማቀቀ ያለው ህብረተሰብችን ምንም ዓይነት አስተማማኝ የሆነ ሃይል እንዲያገኝ ሳይደረግ የሽያጭ ዜና መሰማቱ ወያኔ በአገር እና በወገን ሲቃይ ለመክበር ካለው ራዕይ ተነጥሎ የሚታይ ሴራ አይደለም ይላሉ።

በዚህ ጉዳይ ላይ አስተያየታቸውን ለግንቦት 7 ድምጽ የሰጡት አንድ የቀድሞ መብራት ሃይል ከፍተኛ አክስፐርት ስለ ወያኔ የሃይል ሺያጭ ሲናገሩ "አገዛዙ የኤሌክትሪክ ሃይል ለውጭ አገራት በመሸጥ የሚያገኘው ገንዘብ ከፍተኛ ስለሚሆንና ከሁሉም በላይ መብራቱ የሚሸጥላቸው አገሮች ግዥውን የሚፈጽሙት ደረጃውን በጠበቀ እና አሳሪ በሆነ አለም አቀፍ የንግድ ውል መሰረት ስለሚሆን አቅርቦቱ በውሃ እጥረትም ሆነ በብልሽት ምክንያት ሊቋረጥ ከቻለ አልፎ አልፎ በፈረቃ የምናገኘውንም እስከማጣት ሊያደርሰን ይችላል በማለት ስጋታቸውን ገልጸዋል። አክለውም አሁን በግንባታ ሥራ ላይ ናቸው የሚባሉት ግድቦች በሙሉ እንደተባለው ተጠናቀው አገልግሎት ላይ ከዋሉ እና ሺያጩም እውን ከሆነ ለህዝባችን የሚተርፍ ነገር ካለ የበይ ተመልካችነቱ ወደ መብራት ንግድ ሲዞር ማየቱ ብቻ ነው ብለዋል ። በአምስት አመት የወያነ ትራንስፎርመሽን የወያኔ ሹመኞች አገር አቋራጭ በሆነ የመብራት ሃይል ንግድ አዲስ የዶላር ማግኛ መንገድ ይከፈትላቸዋል፤ የኛው ሚስኪን ህዝብ እንደለመደው እጁን አጣጠፎ እነርሱ ሸራተን ሲንደላቀቁ እና ለአውሮፓም ሆነ አሜሪካ ሃብታሞች እንኳ ያልተዳረሱ ውድ መኪናዎችን ከፊቱ እያሽከረከሩ ስምንሽነሹ ለ20 አመታት ያህል ቁጭ ብሎ እንደታዘበው አሁንም ጨለማውን ታቅፎ "ይህቺንም አታሳጣን አምላኬ" እያለ ረጅም ዕድሜ ለራሱ መማጸኑን ይቀጥላል አለያም ማርም ሲበዛ የመራል ብሎ ይነሳና ለነጻነቱ ፤ ለሰብ አዊ ክብሩና ለአገር የባለቤትነት መብት ወያኔን ተናንቆ ድል ለመቀዳጀት ይነሳል ብሎአል።

## የዘረኛውና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ባለስልጣናት ፌዴራሊዝምን በተመለከተ ቅጥፈት ተያይዘዋል

አምስተኛው አለማቀፍ የፌዴራሊዝም ኮንፈረንስ ባለፈው ማክሰኞና ረቡ ዕ በአዲስ አበባ ውስጥ መካሄዱን አስመልክቶ፤ የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ ያሰፈነው ፌዴራሊዝም ለሌሎች አገራት ምሳሌ እንደሚሆን የአገዛዙ ባለስልጣናት መናገራቸው የገዢው ቡድን ቋሚ ቀጣፊነት አካል ነው ተባለ።

ባለፈው ሳምንት በዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ቁጥጥር ስር ለሚገኘው የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ቃሉን የሰጠው ሹመኛ ሽፈራው ተክለማሪያም፤ እሱ የሚያገለግለው አገዛዝ በኢትዮጵያ ያሰፈነው ፌዴራሊዝም በህዝቦች መካከል የሚነሱ ጥሎችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት አስችሏል፤ በዚህም አገሪቱ ለሌሎች የአፍሪካ አገራት ምሳሌ ትሆናለች ብሏል።

የወያኔ አገዛዝ ስልጣን ከተቆጣጠረበት ጊዜ ጀምሮ፥ ኢትዮጵያ ውስጥ ከዛ ቀደም ታይቶ በማይታወቅ አኳኋን በህዝቦች መካከል ግጭቶች መፈጠራቸው እና አሰቃቂ እልቂቶች እንደተከተሉም ይታወቃል። በርካታ ተመራማሪዎችም አገሪቱ ውስጥ ያለው ሁኔታ ከቀጠለ፣ አንድ ችግር ሲነሳ የእርስ በርስ ግጭት በቀላሉ ሊቀሰቀስ እንደሚችል በመተንበይ ስጋታቸውን በተደጋጋሚ ይገልጻሉ።

ሽፈራው ጨምሮ እንደተናገረው፥ የወያኔ አገዛዝ አሁን በስራ ላይ ያዋለው ስርአት ዴሞክራሲን እና እድገትን የሚያስፋፋ፤ ተሳትፎን የሚያበረታታ እና ብሔር ብሔረሰቦችን የሚጠቅም ነው።

ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ያሉ ብሔር ብሔረሰቦች የወያኔ አገዛዝ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በአገሪቱ ፖለቲካ ውስጥ እውነተኛ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ተፈቅዶላቸው የማያውቅ ሲሆን፤ እራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብታቸውም ባለመከበሩ እስካሁን ድረስ ነፃ ምርጫ ለማካሄድ እና መሪዎቻቸውን ለመምረጥ እንኳ አልቻሉም። በተጨማሪም፥ መዋቅራዊ ዘረኛነትን በማንሰራፋት አገሪቱን በጉልበት የሚገዛው ህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ የአገሪቱን ሃብት አድሎ በተመላበት መንገድ እንደሚያከፋፍል እና የህዝቦቿን የተፈጥሮ ሃብት በመዝረፍ ስራ ላይ ተሰማርቶ እንደቆየ ይታወቃል።

ዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ በአገሪቱ ውስጥ አስፍኜዋለሁ የሚለው እኩልነት ሃሰት በመሆኑም፤ በህዝቦቻቸው ላይ የሚካሄደውን ግፍ እና ኢ-ፍትሃዊነት ለመዋጋት የተነሱ በርካታ የትጥቅ ቡድኖች አሉ። ከነዚህም ውስጥ፥ የኦሮሞ ነፃነት ግንባር፣ የኦጋዴን ብሄራዊ ነፃነት ግንባር፣ የትግራይ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ፣ የቤኒሻንጉል ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ፣ የጋምቤላ ህዝብ ነፃነት ንቅናቄ፣ የሲዳማ ነፃነት ግንባር፣ እና የመሳሰሉት ናቸው።

በሽፈራው ተክለማሪያም ቃል ላይ የዝግጅት ክፍላችን ያናገራቸው የፖለቲካ ተንታኝ፤ ይህ ከአገዛዙ የዘወትር ቀጣፊነት ባህሪ የወጣ አይደለም ብለዋል።

## የአዲስ አበባ ተማሪዎች በአገዛዙ ስለሚካሄድባቸው ግዳጆች ምሬት አሰሙ

የአዲስ አበባ ከተማ ተማሪዎች፥ የወያኔ አገዛዝ በየጊዜው በሚያካሄደው ግዳጆች መሰላቸታቸውን በምሬት ለግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢ ገልጸዋል።

የወያኔ አገዛዝ ከ97ቱ ምርጫ በኋላ ህዝቡን በተለያየ ግዳጅ ወጥሮ መያዙ እና የደርግ ግዜን ትውስታ ማስነሳቱ ይታወቃል። ሰሞኑን፥ የአዲስ አበባ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደ ተለያዩ ማእከላት በግዳጅ ተወስደው የብሔር ብሔረሰቦችን ቀን እንዲያከብሩ ተደርገዋል።

የቦሌና የአካባቢው ተማሪዎች መገናኛ ወደሚገኝ የጎልማሶች ትምህርት ቤት የተወሰዱ ሲሆን፤ ደስተኞች እንዳልነበሩ ለዘጋቢያችን ተናግረዋል። አንዳንዶቹ ተማሪዎች፥ በእሉ እውነት ለብሔር ብሔረሰቦች ክብር ነው ብለው እንደማያምኑ እና በአገዛዙ ቁጥጥር ስር ለሚገኙ መገናኛ ብዙሃን የተቀናበረ የፕሮፓጋንዳ ዝግጅት መሆኑን ገልጸዋል። ወደማያምኑበት በአልም ተገድደው መምጣታቸው ደግሞ ተጨማሪ ንዴት እንደፈጠረባቸው ገልጸዋል።

የተማሪዎቹ ሁኔታ ወያኔ መልካም በማድረግ ሽፋን ስር ለመደበቅ የሚያደርጋቸው ሙከራዎች ሁሉ እየሰሩ እንዳልሆነ እና ህዝቡ የዘረኛውን አገዛዝ እውነተኛ ማንነት መረዳቱን ያሳያል ሲሉ አንድ አስተያየት ሰጪ ለዝግጅት ክፍላችን ገልጸዋል።

## የወያኔ ባለስልጣናት ድጋፍ ለመሰብሰብ ሲሉ በገፍ ያሰጡትን መሬት መልሰው እየቀሙ መሆኑ ታወቀ

በምርጫ 97 ማግስት ጀምሮ ድጋፍ ለማሰባሰብ ሲሉ የአየር ባየር የመሬት ንግድ እንዲስፋፋ የፈቀዱት የወያኔ ባለስልጣናት፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ በጸረ-ሙስና እርምጃ ስም የሰጧቸውን መሬቶች መልሰው መቀማት መጀመራቸው ታውቋል።

ባለፉት አምስት አመታት፥ መሬት ከገበሬዎች በርካሽ ዋጋ እየገዙ በአምስት እና በስድስት እጥፍ የመሸጥ ንግድ በከፍተኛ ሁኔታ መስፋፋቱና ከዚህም ጋር የተያያዘ ሙስና መንሰራፋቱ ይታወሳል። የወያኔ ባለስልጣናት በርካታ ዜጎች እንደዚህ ባለ ሙስና ውስጥ እንዲዘፈቁ በመፍቀድ እና ለራሳቸውም በጉቦ እና በሽርክና ሲጠቀሙ ቆይተዋል። እንዲሁም በእንዲህ አይነቱ ንግድ ውስጥ የገቡ ሰዎች ከአገዛዙ ሊደርስባቸው የሚችለውን ቅጣት በመፍራት ቀጥተኛ ድጋፍ ሲሰጡ እንደነበር ወይም በሚፈጽሙት ግፍ ላይ ዝምተኛነትን በማሳየት አገዛዙን ማጠናከራቸው ይታወቃል።

በነዚህ ዜጎች ላይ በቂ የወንጀል መዝገብ የሰበሰቡት የወያኔ ባለስልጣናት፤ ግለሰቦቹ ከቁጥጥራቸው መውጫ መንገድ እንደሌላቸው ካረጋገጡ በኋላ፤ የራሳቸውን መሬት የማጋበስ ጥማት ለማርካት መነሳታቸው ታውቋል።

የጸረ-ሙስና ኮሚሽን 1.9 ሚሊዮን ካሬ ሜትር መሬት በፍርድ ቤት ማሳገዱን አስመልክቶ ዘጋቢያችን ያናገራቸው የኮሚሽኑ ባልደረባ፤ እርምጃው ከሙስና ጋር የተያያዘ እንዳልሆነ ገልጸዋል። ግለሰቡ እንደሚሉት፥ ጉዳዩ የሙስና ቢሆን ኖሮ፤ አገዳው የሚጀመረው ከአዜብ መስፍን ይዞታዎች ይሆን ነበር። ይልቁንስ እየተካሄደ ያለው፤ ባለስልጣናቱ፥ በተለይም የመለስ ዜናዊ ባለቤት እና ከሷ ጋር የተመሳጠሩት የሚፈልጉት ነገር ነው ብለዋል።

አዜብ መስፍን በሰበታ ከተማ የሚገኙ የመሬት አስተዳደር ሰራተኞችን በስፍራው በግል ተገኝታ ማሳሰሯን ከሳምንት በፊት መዘገባችን ይታወሳል።

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3:00 ሰዓት እስከ 3:30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2:30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት ሬዲዮናችን የመደመጥ ችግር ከገጠመው በድብዳቤ፤ በስልክ ወይም በኢሜል በንቅናቄያችን አድራሻዎች እንድታስታውቁን እንገልጻለን።

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዮን ክፍላችን ወይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዣችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org